# <u>ፍርድና ልመና!</u>

ነጮች አቆርቁዘው ፤ ከጣሉን በኋላ

ምክንያት ሳይኖራቸው ፤ ለማድረስ ብቀላ

አትንኩን ባልናቸው ፤ ክብር አትዳፈሩ!

እንደናንተው ዕዩት ፤ ባልን ተከበሩ!

እንዲህ ካደቀቁን ፤ በክፉ ሸፍጥ ሴራ

በድህነት ሕይዎት ፤ ሆነን የዓለም ጭራ

ለዚህ ካበቃን እጅ ፤ ምንም ምን መቀበል

እርም ቢሆንብንም ፤ መጫን የውርደት ከል

አማራጭ ብናጣ ፤ ድህነቱ ጠንቶ

ሊመጻደቅብን ፤ ምጽዋቱን መጽውቶ

ወርወር ያደርገዋል ፤ በኩራት ተነፍቶ

ምጽዋትም ብቻ አይደል ፤ ብድር ማጥም ከቶ

የተገኘው ዶላር ፤ እንዲያ እርም ተበልቶ

ክብርህ ድሜ ግጦ ፤ ቅስምህ ተንኮታኩቶ

ነጥቆ ቢወስድብን ፤ ጮምጯማ ጅብ መጥቶ

በትንግርት ጋብቻ ፤ ከአህያ ተስማምቶ

የማያገለግል ፤ ብላሸ ሸቀጥ ደፍቶ

ምስቅልቅል የሚዘፍቅ ፤ ሀገር ጠንቅ ግቶ።።

አልቅሰናልና ፤ በእንባ ዓይናችን ጠፍቶ

ጌታ ፈረደ አልኩኝ ፤ ግፋችንን ዓይቶ

ቻይናን ውኃ በላው ፤ የሚለውን ዜና

ደጋግሞ ቢያሰማኝ ፤ ዛሬም ትናንትና

እንደ ሥራው ማግኘት ፤ ከቶ አይቀርምና

አለህ እኮ! ጌታ ፤ አልኩኝ ለምስጋና

ሰማይ አንጋጦጬ ፤ ሰንጥቆ ደመና

መቸ ይሄ ብቻ ፤ አለ ብዙ ገና

ገንዘብ ገንዘብ አትሆን ፤ በግፍ ተከዝና

ከድሀ ሕዝብ አፍ ፤ ዘርፎ ከልመና፡፡

በል በነካው እጅህ ፤ መጽዋቾንም ጎብኘው

ብየም ጸሎት አረኩ ፤ ፈጥኖም እንዲያደርገው

የሥራውን ሰጥተህ ፤ ክንዱን ቁረጥና

ደፍቆ የያዘንን ፤ እንዳንለቅ ልመና

ሽፍጥ ሴራ ማቡኪያውን ፤ እንዳንሆን ደኅና

እርስ በእርስ ተባልተን ፤ ሆነን እንድንቀር መና

ጦቢያ ሰጥማ እንድትቀር ፤ እንዳትወጣ ገንና

እስከወዲያኛውም ፤ ከቶ እንዳትቀና

ይሄንን ጨካኝ እጅ ፤ ክንዱን ቁረጥና

ከደጃቸው አንሣን ፤ አርገኸን ሳተና

ለሥራ አትግተኸን ፤ መልሰህ ልዕልና፡፡

ሰኔ **27 2008** ዓ**.**ም**.**

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

**amsalugkidan@gmail.com**